# መረጃ እና ምላሽ፡ የቤት አከራይዎ የቤት ኪራይ ውዝፍ አለብዎ ቢልዎት እና እርሶም ደሞ የፍርድ ቤት ቀጠሮ ቢኖርብዎ ምን ማድረግ እንዳለብዎ

*የፍርድ ቤት ቀጠሮ ማሳወቂያ* ደርሶት ከሆነ፡ *የቤት ኪራይ ባይከፈል እና አቤቱታ ማቀርብ ቢፈልጉ*፣ ለ ፍርድ ቤት ለምን ቤቱን መልቀቅ እንደሌለብዎ ለማስረዳት ይህንን የመረጃ ወረቀት መጠቀም ይችላሉ። ይህም *ምላሽ* ይባላል። የፍርድ ቤት ወረቀቶቹ ላይ **ግድ** ምላሽ መስጠት አለብዎ። ይህንን ቅጽ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ ይዘዉት በመቅረብ እዚህ ቅጽ ላይ ምልክት ስላደረጉበት ስለ እያንዳንዱ ነገር ለ ፍርድ ቤት ጸሃፊ ወይም ዳኛ ይናገራሉ።

ከታች ተተቀመጠውን ያንብቡ። **ሁሉም** እርሰን የሚመለከቱት ላይ ምልክት ያድርጉ።

1. **አጠቃላይ የእምነት ክህደት ቃል**
   - ☐ በአከራዬ *አቤቱታ* ላይ የተቀመጠው መረጃ ትክክል ይሁን አይሁን የማውቀው ነገር የለም።

2. **ማሳወቂያ እና አገልግሎት**
   - ☐..የቤት ኪራዬን የምክፍልበት ወቅት በ 5 ቀናት እንዳለፈ የሚገልጽ *ማሳወቂያ* እውቅና ባለው *ፖ*ስታ አልደረሰኝም።
   - ☐..የቤት ኪራዬን እንድከፍል *የሚጠይቅ የጽሁፍ ማሳወቂያ አልደረሰኝም*፡
   - ☐..*ኪራይ እንድከፍል የሚጠይቀው ማሳወቂያ* የኪራይ ወራትን እና ያለብኝን ውዝፍ ዕዳ አልገለጸም።
   - ☐..*ኪራይ እንድከፍል የሚጠይቀው ማሳወቂያ* ያለብኝን ውዝፍ ኪራይ ለመከፍል የሚይስችለኝን ቢያስን የ 14 ቀን ማሳወቂያ አልሰጠኝም።
   - ☐ *ኪራይ እንድከፍል የሚጠይቀው ማሳወቂያ* በትክክል ሊደርሰኝ ያልቻለው በሚከተሉት ምክኒያቶች ነው *(መልስ ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም ላይ ምልክት ያድርጉ):*
     - ☐ አከራዩ ራሱ አቀበለኝ።
     - ☐ አከራዩ ለአንድ በኔ ቤት ውስጥ ለማይኖር ወይ ለማይሰራ ሰው ሰጠው።
     - ☐ አከራዩ ቤቴ ውስጥ አስቀመጠው እንጂ በ*ፖ*ስታ አልላከልኝም።
     - ☐ በ*ፖ*ስታ ብቻ ነው የተቀበልኩት።
   - ☐..የ *ፍርድ ቤት ቀጠሮ ማሳወቂያ: ኪራይ ሊከፈል ያልቻለው* እና *አቤቱታው* በትክክል ሊቀርብ ያልቻለው *(መልስ ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም ላይ ምልክት ያድርጉ):*
     - ☐ አልደረሱኝም።
     - ☐ አከራዩ አቀበለኝ።
     - ☐ አከራዩ ለአንድ በኔ ቤት ውስጥ ለማይኖር ወይ ለማይሰራ ሰው ሰጣቸው።
     - ☐ አከራዩ ቤቴ ውስጥ አስቀመጠው እንጂ በ*ፖ*ስታ አልላከልኝም።
     - ☐ በ*ፖ*ስታ ብቻ ነው የተቀበልኳቸው።

3. **እዚህ ጉዳይ ላይ ያሉት ሰዎች** (**ባለድርሻ አካላት**) ***(መልስ ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም ላይ ምልክት ያድርጉ):***
   - ☐ በፍርድ ቤት ወረቀቱ ላይ ስሜ ተብሎ የተቀመጠው**ስህተት** ነው። *ያብራሩ:* ______________________________።
   - ☐ ስሜ በፍርድ ቤት ወረቀቶቹ ላይ የለም፣ ይሁን እንጂ በፍርድ ቤት ወረቀቶቹ የተጠቀሰው አድራሻ ላይ ነው የምኖረው።
   - ☐ በፍርድ ቤት ወረቀቶቹ ላይ የተጠቀሰው ተከራይ**ሞቷል**።
   - ☐ በፍርድ ቤት ወረቀቶቹ ላይ የተጠቀሰው አከራይ የቤቱ ባለቤት **አይደለም** ወይም የቤቱ ባለቤት አይደለም።

4. **ኪራይ** ***(መልስ ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም ላይ ምልክት ያድርጉ):***
   - ☐ ለአከራዩ **ሁሉንም** የኪራይ ገንዘብ ከፍዬዋለው። *መጠን:* $______________________________
   - ☐ ለአከራዩ የኪራዩን **የተወሰነ** መጠን ከፍዬዋለው። *መጠን:* $______________________________
   - ☐ እኔ (ሌላሰው ለኔ ሊከፍልልኝ ሞክረልኝ) ኪራዩን ለመክፈል *ምክርኩ* ነገር ግን አከራዩ ለመቀበል ፍቃደኛ አይደለም።
   - ☐ አከራዩ የጠየቀን: ☐ ከስምምነታችን በላይ የሆነ የኪራይ መጠን ነው።
     ☐ ከኪራይ ስምምነት ውጪ የሆኑ ተጨማሪ ክፍያዎች፣ ዘግይተው የሚደረጉ ክፍያዎች እና/ወይም ቅጣቶች።

5. **የኮቪድ መረጃ** ***(መልስ ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም ላይ ምልክት ያድርጉ):***
   - ☐ ለድንገተኛ የኪራይ ድጋፍ ያስገባሁት ማመልከቻ ገና በሂደት ላይ ነው የሚገኘው። የጉዳዩ ቀነ ቀጠሮ ሊተላለፍ ይገባል።
   - ☐ የድንገተኛ የኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም ለቤት ኪራዬ የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን ለአከራዬ ለመላክ ተስማምቷል።
   - ☐ በ ኮቪድ የተነሳ የገንዘብ ችግር አጋጥሞኛል። አከራዬ የቤት ኪራዬን ባለመክፈሌ ተጠያቂ ሊያደርገኝ ይችላል ነገር ግን ከቤት ሊያስወጣኝ **አይችልም።**

6. **በድጎማ ቤቶች ለሚኖሩ ተከራዮች** ***(መልስ ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም ላይ ምልክት ያድርጉ):***
   - ☐ የኔ ተከራይቼ የምኖርበት ቤት የድጎማ ቤትም እንኳን ቢሆን አከራዩ ግን ይሄንን በፍርድ ቤት ወረቀቶቹ ላይ አልገለጸም።
   - ☐ አከራዬ የመኖሪያ ቤት ኤጀንሲው ከተመነው ኪራይ በላይ ኪራይ እያስከፈለኝ ይገኛል።
   - ☐ አከራዬ የመኖሪያ ቤት ኤጀንሲው የሚከፍለውን የክፍያ መጠን እኔ እንድከፍለው እየጠየቀኝ ይገኛል።
   - ☐ በአፓርትመንቴ ላይ ባለው ችግር ምክኒያት የኔ የቤት ድጎማ ለ አከራዬ እየተከፈለ አይደለም።.
   - ☐ አከራዬ ይሄንን ጉዳይ ከመጀመሩ በፊት☐ እኔን አላሳወቀኝም ወይም የመኖሪያ ቤቶች ኤጀንሲውን
     ☐ ፍቃድ እንዲሰጠው አልጠየቀም።

7. **የኪራይ ንብረት ችግሮች**:
   በኪራይ ንብረቱ ላይ ያሉ ጥገና የሚያስፈልጋቸው ችግሮች ላይ ሁሉ ምልክት ያድርጉ(*አስፈላጊ ከሆነ ተጨማሪ ወረቀቶችን ያያይዙ።*).

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ☐ | ማሞቂያ/መብራት፣ ኤሌክትሪክ | ☐ | ሙቅ ውሃ፣ ወራጅ ውሃ፣ የቧንቧ ውሃ ስራ | ☐ | የሊድ ቀለም | ☐ | ሻጋታ |
| ☐ | በሮች፣ መስኮቶች፣ ምድር ቤቶች፣ ደረጃዎች፣ ሃዲዶች | ☐ | ነፍሳቶች፣ አይጦች፣ ተባዮች፣ | ☐ | የቆሻሻ ማጠራቀሚያ | ☐ | የመገልግለያ መሳሪያዎች |
| ☐ | ሌሎች የኮድ ጥሰቶች/የደህንነት ችግሮች *(ያብራሩ):* | | | | | | |
| ☐ | የመኖሪያ ሰርተፊኬት አለመኖር (C of O) | | | | | | |
| ☐ | የፍርድ ቤት ወረቀቶቹ የተሳሳተ አድራሻ ነው የሚያስቀምጡት። | | | | | | |
| ☐ | የፍርድ ቤት ወረቀቶቹ ቤቴን የሚመለከት ህግ አልገለጹም። | | | | | | |

8. **ሌሎች ምክኒያቶች** ***(መልስ ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም ላይ ምልክት ያድርጉ):***
   - ☐ በመከላከያ ሰራዊት በማገልገል ላይ የምገኝ ነኝ ወይም መከላከያ ውስጥ የሚያገለግል ሰው ጥገኛ ነኝ።
   - ☐ አከራዬ ይህንን ጉዳይ ፋይል ለማድረግ በጣም ብዙ ግዜ ጠበቀ።
   - ☐ አከራዬ ትንኮሳ እያካሄደብኝ ነው። *ያብራሩ:* ______________________________
   - ☐ ሌሎች ምክኒያቶች አሉኝ። *ያብራሩ:* ______________________________

9. **የይገባኛል ጥያቄዎች** (አከራዩ እኔን ሊከፍለኝ ይገባል ) ***(መልስ ሊሆኑ የሚችሉት ሁሉም ላይ ምልክት ያድርጉ):***

☐ አከራዩ እኔን ሊከፍለኝ የሚገባው ቀጠሎ በተጠቀሰው/ሱት ምክኒያት/ቶች ነው:

☐ አስፈላጊ ለነበሩ ጥገናዎች ወይም አገልግሎቶች $________ ከፍያለው።

☐ አከራዩ በህግ ከተገደበለት እኔን ሊያስከፍለኝ ከሚገባው የኪራይ ገንዘበ በላይ $_________ ከፍያለው።

☐ሌሎች ምክኒያቶች። ምክኒያቱን ያብራሩ እና የገንዘቡንም መጠን ይግለጹ፡$___________________________

☐ አከራዩ እኔ ጥያቄ ያቀረብኩባቸው አስፈላጊ የነበሩ ጥገናዎችን ወይም አገልግሎቶችን ያላቀረቡ በመሆናቸው የቤት ኪራይ ገንዘቡን ሊቀንሱልኝ ይገባል።

የቤት መልቀቅ ሂደቱን የተመለከተ መረጃ፣
https://nycourts.gov/courthelp/Homes/evictions.shtml